# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት
## የጥቆማና ምርጫ ማስፈፀሚያ
### የውስጥ መመሪያ/በ2016 ዓ.ም የተሻሻለ/

---

ታህሳስ 6 ቀን 2016 ዓ.ም

**የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ.**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማና ምርጫ ማስፈፀሚያ የውስጥ**

# መመሪያ

## መቅድም

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መምረጥ፣ የምርጫ ሂደቱን የሚያከናውነውን ኮሚቴ ማቋቋም እና ኮሚቴው የሚመራበትን መመሪያ ማጽደቅ ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን በመሆኑ፤
የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን በግልጽነት ማካሄድ የኩባንያ መልካም አስተዳደር ከሚገለፅባቸው መንገዶች መካከል አንዱ በመሆኑ፤
የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ግልጽ፣ ፍትሐዊ እና ተዓማኒ በሆነ መልኩ በማከናወን፣ ባንኩ ብቁ በሆነ አስተዳደር እንዲመራ በማድረግ ረገድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ሚና ወሳኝ በመሆኑ፤
በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጣው የባንክ መልካም አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/71/2019 የባንኩ ባለአክሲዮኖች የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ የሚያቋቁሙበትን አካሄድ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ፣ ምልመላና ምርጫ የሚከናወንበትን ስርዓት የሚደነግግ የውስጥ መመሪያ ማውጣትን እንደ ግዴታ የሚያስቀምጥ በመሆኑ፤
የባንኩ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በብሔራዊ ባንክ የባንኮች መልካም አስተዳደር መመሪያ አንቀጽ 6.1.7 እና በባንኩ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 23(3) (መ) ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ የሚከተሉት ቃላት ከዚህ በታች የተሰጣቸዉን ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

1. "ሠራተኛ" በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ በባንኩ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡

2. "ሰው" ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፡፡

3. "ባንክ" የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ አ.ማ. ነው፡፡

ረቂቅ

4. "ብሔራዊ ባንክ" የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፡፡

5. "ቦርድ" የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

6. "ተጠቋሚ'' ለዕጩነት እንዲወዳደር በባንኩ ባለአክሲዮኖች የተጠቆመ ሰው ነው፡፡

7. "ተደማጭነት ያለዉ ባለአክሲዮን" በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ ከ 2% እስከ 5% ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን ነው፡፡

8. "ኮሚቴ" አባላቱ በጠቅላላ ጉባዔው የተመረጡ የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና አስመራጭ ኮሚቴ ነው፡፡

9. "ዕጩ" በባንኩ ባለአክሲዮኖች ለኮሚቴ አባልነት በጉባኤዉ ላይ የተጠቆመ ወይም ለቦርድ አባልነት ተጠቁሞና በኮሚቴዉ ተመልምሎ ለምርጫ ለጠቅላላ ጉባኤዉ የቀረበ ባለአክሲዮን ማለት ነዉ፡፡

10. "የጉባዔው ስራ አስፈጻሚዎች'' የጠቅላላ ጉባኤውን ስራ የሚያስፈጽሙ፣ አሰያየማቸው እና የስራ ድርሻቸው በባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 20 ስር በዝርዝር የተመለከተው የጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ እና ድምጽ ቆጣሪዎች ናቸው፡፡

11. "ጠቅላላ ጉባዔ/ጉባዔ" የባንኩ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ነው፡፡

## 3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ የሴት ጾታን፤ እንዲሁም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉን ድርጅት ያካትታል፡፡

## 4. ኮሚቴ ማቋቋም

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ የሴት ጾታን፤ እንዲሁም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉን ድርጅት ያካትታል፡፡

1. በሥራ ላይ ያለው ቦርድ የሥራ ዘመን ከመጠናቀቁ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ የባንኩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና አስመራጭ ኮሚቴን ያቋቁማል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት ብዛት 5 (አምስት) ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው የሥራ ዘመን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ የሚካሄድበት መደበኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ሊካሄድ በዳይሬክተሮች ቦርድ ከሚያዘው ቀን 6 ወራት አስቀድሞ ጀምሮ፣ በጉባዔው የተመረጡት ቦርድ አባላት ምርጫ በብሔራዊ ባንክ ሲጸድቅ ይጠናቀቃል፡፡

ረቂቅ

## 5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት

**1.በስራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-**

**ሀ.** የጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ ሲያዝ የኮሚቴ ምርጫ ለማድረግ በአጀንዳ መያዝ፣
**ለ.** የባንኩ የመልካም አስተዳደርን በማረጋገጥ ሂደት ተገቢውን ሚና መወጣት የሚችሉ እና ባንኩ ብቁ  የቦርድ አባላት እንዲኖሩት ለማድረግ የሚሰሩ የኮሚቴ አባላት ነፃ፣ ገለልተኛ እና ግልጽ በሆነ አካሄድ በጠቅላላ ጉባዔ እንዲመረጡ ማስቻል፣
**ሐ.** የኮሚቴው አባላት በዚህ መመሪያ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ አስፈላጊውን ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
**መ.** ኮሚቴው ስራውን በወቅቱ እንዲጀምር ጠቅላላ ጉባዔው የሚደረግበትን የጊዜ ሰሌዳ ለኮሚቴው የማሳወቅ፣
**ሠ.** ለኮሚቴው አስፈላጊውን የገንዘብ፣ የሰው ሀይል እና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ እና
**ረ.** ኮሚቴው በነፃነት ሥራውን እንዲያከናውን ማድረግ፡፡

## 6. አስፈላጊ መስፈርቶች

**1.በኮሚቴ አባልነት የሚመረጥ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-**

**ሀ.** የባንኩ ባለአክሲዮን የሆነ፤
**ለ.** የኮሚቴው አባል ሆኖ ለመስራት ፍላጎት ያለው እና ይህንኑ በጠቅላላ ጉባዔው ዕለት የጉባዔው ስራ አስፈጻሚዎች ተገቢ ነው ብለው በሚወስኑት አመቺ ሁኔታ ለጉባዔው መግለጽ የሚችል፤
**ሐ.** በቂ የስራ ወይም የቢዝነስ ልምድ ያለው፤ ለስራው አስፈላጊውን ጊዜ መስጠት የሚችል፤
**መ.** ባንኩ በሁሉም ረገድ ብቁ የሆኑ የቦርድ አባላት እንዲኖሩት በትጋት፣ በቅንነት እና በታማኝነት ለመስራት ዝግጁ የሆነ፣
**ሠ.** የባንኩ ሠራተኛ ወይም የቦርድ አባል ያልሆነ፣
**ረ.** በትምህርት ደረጃው ቢያንስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለዉ እና
**ሰ.** በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ሀገራት የወጡ ሕጎችን በመተላለፍ በእምነት ማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ያልተፈረደበት፡፡

**2.**የኮሚቴው አባል ሆኖ እንዲመረጥ የሚጠቆመው ድርጅት ከሆነ፤ ድርጅቱን የሚወክለው የተፈጥሮ ሰው ማንነት እና የስራ ልምዱ፣ እንዲሁም ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከቱትን መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑ ድርጅቱን ወክሎ በጉባዔው ላይ በተገኘው ሰው ለጉባኤው መገለጽ አለበት፡፡

## 7. የኮሚቴው አባላት ስብጥር

**1.** በተቻለ መጠን ተገቢ የሆኑ ሕጎችና ደንቦችን ለመተግበር፣ የመረጃ ቴክኖሎጂን ስራ ላይ ለማዋል እንዲሁም የባንክ ኩባንያ አስተዳደርን በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በአስተዳደር፤ በአመራር፤ በሕግ እና በመረጃ ቴክኖሎጂ ላይ እውቀቱና ልምዱ ያላቸውን በኮሚቴው ለማካተት ጥረት መደረግ አለበት።
**2.** በጉባኤው ከሚጠቆሙት 10 (አስር) ዕጩዎች ውስጥ ቢያንስ 4 (አራቱ) ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች ይጠቆማሉ።
**3.** ከ4 (አራቱ) ተደማጭነት የሌላቸዉ ዕጩዎች ውስጥ በጉባዔው ከፍተኛ ድምፅ ያገኙ የመጀመሪያዎቹ 2 (ሁለቱ) ይመረጣሉ/ይወሰዳሉ።
**4.** ቀሪዎቹ 3(ሶስቱ) የኮሚቴው አባላት በሁሉም (ተደማጭነት ባላቸዉ እና ተደማጭነት በሌላቸዉ) ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙት ውስጥ ባገኙት ድምጽ ቅደም ተከተል መሰረት ይመረጣሉ/ይወሰዳሉ።
**5.** በስራ ላይ የሚገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የኮሚቴ አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም።

## 8. የኮሚቴው ምርጫ አካሄድ

**1.** የኮሚቴ አባላት ምርጫ የሚከናወነው ለዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በንግድ ሕግ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ነው። በዚሁ መሠረት በንግድ ሕጉ እና በባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 20 አግባብ የተሰየሙ የእለቱ የጉባዔው ስራ አስፈጻሚዎች ምርጫውን ይመሩታል።
**2.** ጠቅላላ ጉባዔው የኮሚቴውን አባላት ሲመርጥ ስራቸው እና ኃላፊነታቸው በባንኩ መልካም አስተዳደር ውስጥ የሚኖረውን ወሳኝ ሚና፤ እንዲሁም አባላቱ ያላቸውን ልምድ፣ እውቀት እና መልካም ስማቸውን ባገናዘበ መልኩ መሆን አለበት።
**3.** ጉባኤው 10 (አስር)ዕጩዎችን በመጠቆም ከዚህ ውስጥ በሚያገኙት ድምፅ ብዛት ቅደም ተከተል መሠረት 5 (አምስቱ) የኮሚቴው አባላት ሆነው እንዲሰሩ ይመርጣቸዋል። ዕጩዎቹ ያገኙት የድምጽ ብዛት እኩል በሚሆንበት ጊዜ የጉባዔው ስራ አስፈጻሚዎች በጋራ በመሆን የዕጩዎቹን ልምድ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ጾታ  እና ሌሎች በበቂ ምክንያት አግባብ ናቸዉ ብለው በሚስማሙባቸዉ መስፈርቶች መሰረት ይለዩዋቸዋል።
**4.** በዕጩነት ቀርበው በጉባኤው ለኮሚቴው አባልነት ያልተመረጡት ቀሪዎቹ ዕጩዎች ባገኙት ድምፅ ቅደም ተከተል መሠረት በተጠባባቂነት ይያዛሉ።
**5.** ጠቅላላ ጉባኤው የኮሚቴ አባላቱን የሚመርጠው ምስጢራዊ በሆነ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ነው። አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ከተገኘ ምስጢራዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ምርጫው በኮምፒውተር በታገዘ ስርዓት ሊከናወን ይችላል።
**6.** የምርጫው ውጤት ምርጫው በተካሄደበት ዕለት ለጉባዔው ይገለፃል። ይህ ካልተቻለ በርዱ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በዋናው መስሪያ ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ውጤቱን በመለጠፍና በባንኩ ድህረ-ገጽ ላይ በመልቀቅ ዉጤቱን መግለፅ አለበት።
**7.** እንዲሁም እያንዳንዱ የኮሚቴ ተመራጭ እና ተጠባባቂ በቦርድ ሰብሳቢ ተፈርሞ በሚላክለት/በሚደርሰዉ ደብዳቤ የምርጫ ዉጤቱን  እንዲያዉቅ ይደረጋል።

## 9. የኮሚቴው ኃላፊነቶች

**ኮሚቴው የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉት፡-**

**1.**ኮሚቴው ከሚመለከተዉ የባንኩ አካላት ጋር በመሆን የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫን ሙሉ ሂደት የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።
**2.** ሥራውን ከመጀመሩ አስቀድሞ ከመሃከሉ የኮሚቴውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የመምረጥ፣ እንዲሁም ይህንኑ ስራ ላይ ላለዉ ዳይሬክተሮች ቦርድ በማሳወቅ የስራውን መርሐ ግብር (የጊዜ ሰሌዳ) መንደፍና ስራዉን መጀመር፤
**3.**ስለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ፣ ምልመላና ምርጫ ሂደት አተገባበር በዚህ መመሪያ በተደነገጉት እና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በባንኩ የሚሰጠዉን ስልጠና የመዉሰድ፤
**4.** አግባብነት ባለው የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ዕጩዎች የሚጠቆሙበትን ሥርዓት መዘርጋት እና ተጠቋሚዎችን መቀበል፤
**5.** የጥቆማና የምርጫ ሂደት ግልፅና ቀላል በሆነ መንገድ እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
**6.** የምርጫ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት አጠቃላይ ስለምርጫው አካሄድና በመራጮች /በተሳታፊ ባለአክሲዮኖች/ ሊወሰዱ ስለሚገባቸዉ ጥንቃቄዎች ለጉባኤዉ በቂ ማብራሪያ መስጠት፤
**7.** ባጠቃላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ ሙሉ ሂደቱን አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች፣ የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፣ በባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ እና በዚህ የዉስጥ መመሪያ መሰረት፤ እንዲሁም ግልጽ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒ በሆነ መንገድ በአግባቡ የማከናወን፤ እና ይሄንኑ ለጉባኤው በሚያቀርበው ሪፖርት የማረጋገጥ።

## 10. የኮሚቴው አሠራር

**1.** ኮሚቴው ጊዜያዊ ቢሮ እና እንደአስፈላጊነቱ የባንኩን ነባር ሰራተኞች እና/ወይም ለኮሚቴው ስራ የሚቀጠሩ አዲስ ጊዜያዊ ሠራተኞችን በመያዝ ሥራውን ያከናውናል።
**2.** ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ የሚሰበሰብበትን ቦታ፣ ቀንና ጊዜም ኮሚቴዉ በራሱ ይወስናል።
**3.** አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኮሚቴው ሰብሳቢ አስቸኳይ የኮሚቴ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
**4.** ከግማሽ በላይ የሆኑ የኮሚቴው አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሟላል።
**5.** የኮሚቴው ውሣኔ ተፈፃሚ የሚሆነው በአባላቱ ተራ የድምጽ ብልጫ ሲደገፍ ነው። ሆኖም እኩል ድምጽ ሲኖር ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
**6.** የኮሚቴው ሰብሳቢ ኮሚቴውን የመምራት፣ አጀንዳ ቀርጾ ስብሰባ የመጥራትና የመምራት፣ እንዲሁም ኮሚቴውን በመወከል ግንኙነቶች የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ፀሐፊው የኮሚቴውን ቃለ ጉባዔ የመያዝ እና ቃለ ጉባዔው በአግባቡ መቀመጡን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

ረቂቅ

**7.** ኮሚቴው በስብሰባው ያደረጋቸው ውይይቶች አጭር ቃል እና የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች በቃለጉባዔ መያዝ ያለባቸው ሲሆን ቃለጉባዔውም ተገቢው ቁጥር ተሰጥቶት በስብሰባ በተገኙ አባላት መፈረም አለበት፡፡
**8.** አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ኮሚቴው አስተማማኝ በሆነ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ስብሰባ ለማካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም የኤሌክትሮኒክ ዘዴው የተሰብሳቢዎችን ማንነት መለየት፣ ተሰብሳቢዎችን በአንድ ጊዜ ማሳተፍ፣ ድምጽና ምስል ሳይቆራረጥ ማስተላለፍ፣ የስብሰባውን ምስጢር መጠበቅ፣ በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ አስተያየትና ድምጽ መስጠት እንዲሁም የሚሰጠውን ድምጽ በተገቢው ሁኔታ መቁጠር የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
**9.** ከኮሚቴው አባላት መካከል ቁጥራቸው ከግማሽ (50%) በታች የሆኑት የኮሚቴውን ሥራ ቢለቁ የተቀሩት አባላት ስራውን በለቀቁት ምትክ በተጠባባቂነት ከተያዙት ውስጥ በምርጫ ጊዜ በተሰጣቸው ድምፅ ቅደም ተከተል መሠረት ይተካሉ፡፡ ኮሚቴዉ ይህንኑ ለባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በደብዳቤ ያሳዉቃል፡፡
**10.** በስራ ላይ ያለው ኮሚቴ የአባላቱ ቁጥር ከግማሽ (50%) በታች በሆነ ጊዜ ግን ቀሪዎቹ የኮሚቴ አባላት ጉዳዩን በስራ ላይ ላለው የዳይሬክተሮች ቦርድ በማሳወቅ ሥራውን መተው አለባቸው፡፡
**11.** በንዑስ አንቀጽ 10 መሠረት ኮሚቴው ስራውን ከተወ በሥራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ይሄንኑ ለብሔራዊ ባንክ ያሳዉቃል፡፡ በጠቅላላ ጉባኤው ቀንም ለጉባኤው በማሳወቅ በዕለቱ አስመራጭ ኮሚቴ በማስመረጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እንዲመረጡ ያደርጋል፡፡
**12.** ኮሚቴው ግዴታዎቹን ግልጽ፣ ፍትሐዊ እና ተዓማኒ በሆነ መልኩ ባለመወጣቱ፤ ወይም የጥቆማና የምርጫ ሂደቶችን ሲያከናዉን አግባብነት ያላቸዉን ሕጎች፤ የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና/ወይም ይኽን የዉስጥ መመሪያ በመጣሱ ምክንያት የተደረገዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በብሔራዊ ባንክ ከተሰረዘ፤ የገንዘብ መጡኑ ለአባላቱ ለአገልግሎት ክፍያ እስከሚከፈላቸዉ ጣሪያ

## 11. የጥቆማ ጥሪ አደራረግ

**1.** ኮሚቴው ባለአክሲዮኖች ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የዕጩዎች ጥቆማ እንዲያደርጉ ሰፊ ስርጭት ባለው እና ምቹ በሆነ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴ ጥሪ ማስተላለፍ አለበት፡፡ ጥሪው የሚተላለፍበት መገናኛ ብዙሃን በኮሚቴው የሚወሰን ሆኖ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ስልቶችን፣ እንደ ድህረ ገጽ፣ የባንኩ የተረጋገጡ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች፣ አጭር የጽሑፍ መልዕክት (SMS)፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር፣ ኢ-ሜይል፤ የባንኩን ቅርንጫፎችና ... ወዘተ ለመጠቀም ይችላል፡፡ ሁሉም ባለአክሲዮኖች ጥቆማ ሲያደርጉ የተሻለ የመጠቆሚያ ዘዴ እንዲጠቀሙ ኮሚቴው ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡
**2.** ኮሚቴው ጥሪውን ሲያስተላልፍ ተጠቋሚዎች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች እና ጥቆማው የሚቀርብበትን ፎርም ማሳወቅ አለበት፡፡
**3.** ኮሚቴው የጥቆማ ጊዜ የሚጀምርበትን እና የሚያበቃበትን ቀን መግለጽ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ለጥቆማው የሚሰጠው ጊዜ ከሦስት ወራት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡
**4.** ኮሚቴው ዕጩዎችን እንዲጠቁሙ ለሁሉም ባለአክሲዮኖች እድል መስጠት አለበት፡፡ ነገር ግን አንድ ባለአክስዮን መጠቆም የሚችለው አንድ ዕጩ ብቻ ነው፡፡

## 12. የተጠቋሚዎች ምዝገባ እና የዕጩዎች ስብጥር

**1.** ኮሚቴው መዝገብ በማዘጋጀት ተጠቋሚዎችን በመዝገቡ ይመዘግባል፡፡ የተጠቋሚዎችን ምዝገባ በኮምፒዩተር ሲስተም በታገዘ ስርዓትም ሊያከናውን ይችላል፡፡
**2.** የኮሚቴው አባል በሥራ ዘመኑ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ሊጠቆም ወይም ዕጩ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡
**3.** ተጠቋሚው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ሲሆን ድርጅቱን የሚወክለው የተፈጥሮ ሰው ማንነት በጥቆማው ምዝገባ ጊዜ በዝርዝር ለኮሚቴው በተጠቋሚው ድርጅት መገለጽ ይኖርበታል፡፡
**4.** አጠቃላይ የዕጩዎች ብዛት 22 (ሃያ ሁለት) ሲሆን ተጨማሪ 6 (ስድስት) ተጠቋሚዎች በተጠባባቂ ዕጩነት ይያዛሉ፡፡
**5.** ከአጠቃላይ ዕጩዎች መካከል 1/3ኛ 8(ስምንቱ)፣ እንዲሁም ከተጠባባቂዎቹ ቢያንስ 2 (ሁለቱ) ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች የተጠቆሙ መሆን አለባቸው፡፡
**6.** ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 የተጠቀሰውን ስብጥር ለመጠበቅ 2/3ኛዉ (14ቱ) ዕጩ ተጠቋሚዎች በሁሉም (ተደማጭነት ባላቸዉና እና ተደማጭነት በሌላቸዉ) ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙት ይወሰዳሉ፡፡
**7.** ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 የተጠቀሰው ስብጥር ባይሟላ ኮሚቴው ስብጥሩ እንዲኖር ለማድረግ ተገቢውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡ ለዚሁ ይረደው ዘንድ ኮሚቴው በቅድሚያ 1/3ኛ ዕጩዎችን በተናጠል ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙት ውስጥ ካስመረጠ በኋላ፤ 2/3ኛውን ደግሞ በሁሉም (ተደማጭነት ባላቸዉ እና ተደማጭነት በሌላቸዉ) ባለአክሲዮኖች ከተጠቆሙት ያስመርጣል፡፡

## 13. የዕጩዎች ምልመላ እና ለጉባዔው የሚቀርቡበት ሁኔታ

**1.** ኮሚቴው ከተጠቋሚዎች ውስጥ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚያቀርባቸውን ዕጩዎች የሚመለምለው ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሕጎች፣ መመሪያዎች እና በባንኩ የመመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ሲሆን፣ የሂደቱን ግልፅነትና ተዓማኒነት በሚያረጋግጥና ለጠቅላላ ጉባኤው የተሻሉ እንዲሁም ብቁ ዕጩዎች እንዲቀርቡ በሚያስችል መልኩ ከሕጉ ጋር የማይጋጩ የራሱን ተጨማሪ መለያ መስፈርቶችም ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
**2.** ተፈጻሚነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና በባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሴቶች ከተጠቆሙ፣ ኮሚቴዉ በዕጩዎች ተካተዉ ለምርጫ ለጉባኤዉ እንዲቀርቡ ጥረት ያደርጋል፡፡
**3.** ኮሚቴዉ ከተጠቋሚዎች መካከል የዕጩዎችን ምልመላ ሲያደርግ ተጠቋሚዎች እኩል ነጥብ ካገኙ፤ የተጠቋሚዎችን የትምህርት ደረጃ፤ የትምህርት ዘርፍ፤ የስራ ልምድና ሌሎች ኮሚቴዉ በበቂ ምክንያት አግባብ ናቸዉ ብሎ በሚያወጣቸዉ መስፈርቶች መሰረት ይለያቸዋል፡፡ ሆኖም ነጥባቸዉ እኩል ከሆኑት ተጠቋሚዎች ዉስጥ ሴት የምትገኝ ከሆነ ለእርሷ ቅድሚያ ሊሰጣት ይገባል፡፡
**4.** ኮሚቴው ቢያንስ ባለአክሲዮኖች የቦርድ አባላቱን የሚመርጡበት ጠቅላላ ጉባዔ ከመካሄዱ አንድ ወር በፊት የመለመላቸውን ዕጩዎች ዝርዝር በሚከተሉት ሁኔታዎች መግለፅ አለበት፡-

**ሀ.** በባንኩ ዋና መስሪያ ቤትና ቅርንጫፎች ሁሉም ሰው በሚያየው ቦታ እንዲለጠፍ ያደርጋል፤
**ለ.** ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ እንዲወጣ ያደርጋል፤
**ሐ.** እንዲሁም በባንኩ ድረ-ገጽ ላይ በማውጣት ለተቃውሞና እና ለቅሬታ ከ2 (ሁለት) ሳምንታት ያላነሰ ጊዜ መስጠት አለበት፤ በዚሁ መሰረትም በበቂ ምክንያት ተደግፎ የቀረበ አሳማኝ ተቃውሞ ወይም ቅሬታ ካለ ይህንኑ ከግምት በማስገባት ተወዳዳሪ ዕጩዎችን በድጋሜ ሊለይ ይችላል፡፡

**5.** ኮሚቴው የዕጩዎችን ዝርዝር ለጠቅላላ ጉባኤው ማቅረብ አለበት፡፡ የዕጩዎች ዝርዝር ሲቀርብም ዝርዝሩ ቢያንስ የሚከተለውን መረጃ መያዝ አለበት፡-

**ሀ.** የዕጩውን ስም እና እድሜ፤
**ለ.** የትምህርት ደረጃ እና የትምህርት ዘርፉ፤
**ሐ.** የሥራ ልምድ፤
**መ.** መረጃው በተሰጠበት ወቅት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት ካለው ይህንኑ መጥቀስ፣ ድርጅት ከሆነ የተወካዩን፤
**ሠ.** ዕጩዎቹ የተመለመሉበት መስፈርት እና ሙሉ የምልመላ ሂደቱን የሚመለከት ሪፖርት፤
**ረ.** ከላይ ከ "ሀ" እስከ "ሠ" የተጠቀሱት መስፈርቶች ዕጩ ተወዳዳሪው ድርጅት እንደሆነ ድርጅቱን እንዲወክል የተሰየመውን የተፈጥሮ ሰው ያገናዘቡ ይሆናል፡፡

**6.** ለጉባኤዉ የቀረበዉ የዕጩዎች ዝርዝር በሃገሪቱ ሕጎች፣ በባንኩ የመመስረቻ ጽሑፍ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹ መስፈርቶችን በአግባቡ ማሟላቱን ኮሚቴው ለጉባዔው ማረጋገጥ አለበት፡፡

**7.** በኮሚቴው በተደረገ የጥቆማ ጥሪ መሰረት የቀረቡ ተጠቋሚዎች ባይኖሩ ወይም በዚህ መመሪያ ከተቀመጠዉ ቁጥር በታች ከሆኑ ወይም ተጠቋሚዎቹ በሕጉ፤ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም በባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ የተቀመጡ መስፈርቶችን ካላሟሉ ኮሚቴው የባንኩን ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳኋን በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን የዕጩዎችን ቁጥር 22(ሃያ ሁለት) እና6(ስድስቱ) ተጠባባቂዎችን ግልፅነት፣ ፍትሃዊነትና ተዓማኒነት ባለው መልኩ በመመልመል ራሱ ያዘጋጃቸውን ዕጩዎች ዝርዝርና መስፈርቶች ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 ስር በተጠቀሰው አግባብ ከበቂ ማብራሪያ ጋር ለጠቅላላ ጉባኤው ለምርጫ ያቀርባል፡፡

**8.** ከላይ በአንቀጽ 11 እና/ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ስር በኮሚቴው የተደረጉ ጥረቶች የሚፈለገውን የዕጩዎችንና የተጠባባቂዎችን ቁጥር ማስገኘት ካልቻለ፣ ኮሚቴው ይህንኑ ጉባኤጉው ከመካሄዱ አንድ ወር ቀደም ብሎ ለቦርድ በማሳወቅና ለጉባኤውም ሪፖርት በማድረግ በጠቅላላ ጉባኤው ዕለት የተጓደለን የዕጩዎች ቁጥርና ተጠባባቂዎች ጥቆማ/ምርጫ ያካሂዳል፡፡

ረቂቅ

## 14. የቦርድ አባላት ምርጫ ቅድመ ዝግጅት

**1.** ኮሚቴው ከጉባኤው ስራ አስፈጻሚዎች ጋር በመሆን የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደትን የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡
**2.** ኮሚቴው ከሚመለከታቸው የባንኩ አካላት ጋር በመሆን የድምፅ መስጫ ካርድ፣ የምርጫ ሳጥኖችን እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያዘጋጃል፡፡
**3.** የድምፅ መስጫ ካርዱ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-
**ሀ.** የባለአክሲዮኑን ሙሉ ስም፣
**ለ.** የባለአክሲዮኑን የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት/መጠን፣
**ሐ.** የባለአክሲዮኑን የመለያ ቁጥር፣
**መ.** የባንኩን ስም እና አርማ፣
**ሠ.** የባንኩን ማህተም፤
**ረ.** ባለአክሲዮኑ ሊመርጠው የሚፈልገው ዕጩ ስም ወይም መለያ ቁጥር/ኮድ/ የሚፃፍበት ቦታ፤
**ሰ.** ባለአክሲዮኑ የሚፈርምበት ቦታ፤
**ሸ.** ባለአክሲዮኑ ምርጫዉን የሚገልጽበት ምልክትና ሲመርጥ ሊወስድ ስለሚገባዉ ጥንቃቄ የሚያወሳ ማሳሰቢያ፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ካሉ በካርዱ ላይ ሊካተቱ ይገባል፡፡
**4.** ኮሚቴው ተደማጭነት የሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች ለምርጫ የሚጠቀሙበትን የምርጫ ካርድ ከሌላዉ (ተደማጭነት ያላቸዉ እና ተደማጭነት የሌላቸዉ በጋራ ከሚጠቀሙበት) በቀለም ተለይቶ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት፡፡
**5.** በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ላይ የመገኘት ፊርማ /አቴንዳንስ/ በሚወሰድበት ጊዜ የድምፅ መስጫ ካርዶች ለባለአክሲዮኖቹ ይሰጣሉ፡፡
**6.** ኮሚቴው ዕጩዎችን በተመለከተ በአንቀጽ 13(5) ስር የተገለጸውን ዝርዝር የያዘ መረጃ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡
**7.** ኮሚቴው ተገቢ ነው ብሎ በሚያስቀምጠው አመቺ ሁኔታ ዕጩዎች ራሳቸውን ለጉባዔው እንዲያስተዋውቁ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ለመስራት ፍቃደኛ መሆናቸዉን እንዲገልፁ ለዕጩዎቹ እድል መስጠት አለበት፡፡
**8.** ከዕጩዎች መካከል የቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ ፈቃደኛ የማይሆን ቢኖር ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ጥቆማው ተቀባይነት ካጣ በተጠባባቂነት ከተያዙት ዕጩዎች በቅደም ተከተል በመተካት ምርጫው እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

## 15. የድምፅ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

ረቂቅ

**1.** በምርጫው ዕለት ኮሚቴው የድምጽ መስጫ ሳጥኖችን እና ሌሎች ለምርጫው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ለምርጫው አመቺ በሆነ መልኩ አዘጋጅቶ ያስቀምጣል፡፡

**2.** ባለአክሲዮኖች በድምጽ መስጫ ካርድ ላይ የሚመርጡትን ዕጩ ስም ወይም መለያ ቁጥር/ኮድ/ ለዚሁ ተግባር በተሰጠው በታ ከጻፉ በኋላ በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ያስገባሉ፤ ወይም ምስጢራዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በኮምፒውተር በታገዘ ስርዓት ምርጫውን ያከናውናሉ፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተመለከተው መሰረት ለመፈጸም ኮሚቴው የአካል ጉዳተኞችን የባለአክሲዮንነት መብታቸውን እንዲጠቀሙ በማስተናገድ ረገድ አመቺ እና አጋዥ ሁኔታን ያመቻቻል፡፡

**3.** የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ እንደተጠናቀቀ ኮሚቴው ከጉባዔው ስራ አስፈጻሚዎች እና ቦርዱ የኮሚቴውን ስራ እንዲያግዙ ካስመደባቸው የባንኩ ሠራተኞች ጋር በመሆን የድምፅ ቆጠራ ያካሄዳል፡፡

**4.** ኮሚቴው ለእያንዳንዱ ዕጩ የተሰጠውን ድምጽ እና ውድቅ የተደረጉ የድምጽ መስጫ ካርዶችን ከነምክንያታቸዉ መመዝገብ አለበት፡፡ የኮሚቴው አባላት ወድቅ የተደረጉ የምርጫ ካርዶችን በፊርማቸው ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

**5.** የድምጽ መስጫ ካርድ በሚከተሉት ምክንያቶች ውድቅ ይደረጋል፡-

- **ሀ.** የባለአክሲዮኑን ስም የማያመለክት ከሆነ፤
- **ለ.** የባለአክሲዮኑን የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት/መጠን/ የማያመለክት ከሆነ፤
- **ሐ.** የባንኩ ስም እና አርማ ያልታተመበት ከሆነ፤
- **መ.** የዕጩ ስም/መለያ ቁጥር/ ያልተፃፈበት ከሆነ፤
- **ሠ.** የመራጩ ፊርማ የሌለበት ከሆነ፤
- **ረ.** ይዘቱን ለመለየት አዳጋች የሚያደርግ ስርዝ ድልዝ ያለበት ከሆነ፤
- **ሰ.** የባለአክሲዮኑን መለያ ቁጥር የማያመለክት ከሆነ፤

**6.** በምርጫ ካርዱ ላይ ከተቀመጠው ስፍራ በማለፍ አልያም ከተቀመጠው መስመር አልፎ በመጨመር የተካተቱ (የተጨመሩ) ዕጩዎች ግንዛቤ ውስጥ አይገቡም፡፡ ይሁንና ይህ ብቻውን የምርጫ ካርዱን ሙሉ ለሙሉ ውድቅ አያደርገውም፡፡

**7.** የድምፅ ቆጠራዉ እንደተጠናቀቀ፣ የኮሚቴዉ አባላት የድምፅ አሰጣጡና የቆጠራዉ ሂደት በትክክል መካሄዱን እና የቆጠራው ውጤትም ትክክል መሆኑን ለዚሁ ዓላማ በሚዘጋጅ ቃለጉባኤና ቅፅ ላይ በመፈረም ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

**8.** ኮሚቴዉ የተቆጠሩት የድምፅ ካርዶች ታሽገዉ ለብቻ እንዲያዙ/እንዲቀመጡ/ያደርጋል፡፡

**9.** የድምፅ ቆጠራው ውጤት ድምጽ በተሰጠበት ቀን ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በኮሚቴዉ ይገለፃል፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን በቀጣዩ የሥራ ቀን በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ እንዲሁም በባንኩ ድህረ-ገጽ ላይ በማውጣት መገለጽ አለበት፡፡

## 16. ወጪዎች

**1.** የኮሚቴው የዕለት ተዕለት የሥራ ወጪዎች በባንኩ ይሸፈናሉ፡፡
**2.** የኮሚቴው አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት ባንኩ ሊከፍል የሚገባውን ወርሃዊ የትራንስፖርት አበልና የምርጫ ውጤቱ በብሔራዊ ባንክ ሲጸድቅ የሚከፈላቸውን የአገልግሎት ክፍያ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይወስናል፡፡ ጉባኤዉ ይህንን ሲወስን የኮሚቴውን የስራ ጊዜ ርዝማኔና የሚሰጡትን አገልግሎት ከግምት ማስገባት አለበት፡፡
**3.** አንድ የኮሚቴ አባል የኮሚቴው የሥራ ጊዜ ሲጠናቀቅ ከላይ የተመለከተው ጥቅል የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈለው አባሉ ቢያንስ የኮሚቴውን ሥራ ከመቶ ሰባ አምስት እጅ (75%) የተሳተፈበት እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

## 17. መመሪያው ተፈፃሚነት የሚያጣባቸው ሁኔታዎች

**1.** ስራ ላይ ካሉት የቦርድ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በሚከተሉት ምክንያቶች ከኃላፊነታቸው ከለቀቁ/ከተነሱ/ ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡-

- **ሀ.** የስራ ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት በጠቅላላ ጉባዔ ወይም በብሔራዊ ባንክ ከስራቸው እንዲነሱ ከተደረጉ፣
- **ለ.** በገዛ ፈቃዳቸው ከቦርድ አባልነት ከለቀቁ፣
- **ሐ.** በማንኛውም ምክንያቶች በቦርድ አባልነት መቀጠል ካልቻሉ፣ ወይም
- **መ**. በኮሚቴው የቀረቡ ዕጩዎች ከመቶ ሃምሳ እጅ (50%) በላይ በሆነ ድምጽ በጠቅላላ ጉባኤው ተቀባይነት ካጡ፡፡

**2.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ-ሐ) ስር እንደተገለጸው ከስራ የለቀቁ/የተነሱ/ የቦርድ አባላት ቁጥር ከቦርድ ቁጥር አንፃር ከግማሽ በላይ ከሆነ፣ በስራ ላይ የቀሩት የቦርድ አባላት በ30 (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት ተፈጻሚነት ባላቸው የንግድ ሕጉ እና የባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ ድንጋጌዎች መሰረት በጎደሉት አባላት ምትክ ምርጫ እንዲከናወን ማድረግ አለባቸው፡፡

**3.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) ስር የተገለጸው ከተከሰተ ጉባኤዉ በዕለቱ አዲስ አስመራጭ ኮሚቴ ይመርጣል፡፡ አዲስ የተመረጠዉ አስመራጭ ኮሚቴም ተፈጻሚነት ባላቸው የንግድ ሕጉ እና የባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ ድንጋጌዎች መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ያካሂዳል፡፡

**4.** በማንኛውም ምክንያት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከተጓደለ እና በስራ ላይ የቀሩት አባላት ከመቶ ሃምሳ እጅ(50%) ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ፤ የተጓደሉትን ዳይሬክተሮች ቀሪ ጊዜ የሚሸፍኑ ሌሎች ዳይሬክተሮች ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ባገኙት ድምጽ ቅደም ተከተል መሰረት በመተካት ሹመቱ እንዲጸድቅ በ30 (ሰላሣ) የስራ ቀናት ውስጥ ለብሔራዊ ባንክ ያቀርባሉ፡፡

ረቂቅ

## 18. ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ስለማዘጋጀት

ኮሚቴው ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት የሚረዳ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ (Guideline) በማዘጋጀት ስራ ላይ ማዋል ይችላል።

## 19. ተፈጻሚነት ስላላቸው ሕጎች

ይሄንን መመሪያ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች፣ የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና የባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ አግባብነት ያላቸው አናቅጽ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## 20. ስለመተካት

በባለአክሲዮኖች 16ኛ መደበኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ ከታህሳስ 17 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የነበረዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የዕጩዎች የጥቆማ እና የምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ ተሻሽሎ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

## 21. መመሪያዉን ስለማክበር

ኮሚቴዉ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀዉን ይኽንን የዉስጥ መመሪያ በጥብቅ ማክበር አለበት።

## 22. ማሻሻያ

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጥቆማ እና ምርጫ ማስፈፀሚያ መመሪያ ተፈጻሚነት ካለው ሕግ ጋር በማይቃረን መልኩ በጠቅላላ ጉባኤው ሊሻሻል ይችላል።

## 23. ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ከፀደቀበት ከታህሳስ 6 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ረቂቅ